# አውቆ የተኛ

አውቆ የተኛ ልግመኛ
ፀረ-ሰላም አድመኛ
ዓይነ-ሥውር ልበ-ብርሃን
ልበ-ስውር ዘመነ-ጭፍን
መልካም ከማያስተወል ልብ
ይሻል የለ ዓይነ-ግብ።
ጠብ ይሻል አሉ ዳግማዊ
ብሔረ-ሲኦላዊ
ታወረ አሉኝ ላለማየት
ልቦናውን ሸፍኖት
ደግነቱን ነፍጎት
ሰላም ከውስጡ ጠፍታ
ተፈጥሮበት ሁካታ
ይቃዣል አሉኝ በጸና
ዛሬም እንደገና
እንዴት ብዬ ልንገረው እሱን
የመረጠ ጥፋትን
የሰላም ጠላትን
እንዴት ልቀስቅሰው እርሱን
አውቆ የተኛውን።
የሚሰማቸው ካሉት
ንገሯቸው ይንገሩት
ድህነት መሰይጠኑን
የአገር እድገት ማገዱን
የእኛን ውጊያ መፈለጉን
ጠላታችን ለእኛ ድህነት
የምንዋጋው ዕለት ዕለት
ዳግማዊ የማያወቀው
መስማት ያልፈልገው
ማየት የተሳነው
ጠላታችን ድህነት ነው።
ማን ይፈልጋል ዳግማዊን
ይጋግር እንጀራውን-የህልሙን
ይጋልብ እራሱን-የምኞቱን
የጥፋት ፈረሱን
እኛስ ተጉዘናል ወደፊት
ከዚህ በኋላ ወዴት።
አንተ ትናንትን ናፍቀህ
ዛሬ ታወርኩ ትላለህ
ልፀልይህ አስቤ
ከልቤ
ጀመርኩ ፀሎቱን

እውነቱን
ደግሞ ተወኩት ፀሎቱን
አየውህና በህሊናዬ
ክፋትህን ከደግ ከፍዬ
ባሰላሰለው ውጤቱን
የፀሎቴን
ተነሳሁ ትቸው መማለዴን
ነቅፌ ድርጊቴን
ሰው እንዴት ለአንተ ይጸልያል
ለፈረሰ-ሳጥናኤል
ጥፋት ለሚመኝ ለሃገር
ሃውርያ-ዲያብሎስ ግብረ ነውር።
አብረን እንሥራ እንደግ
ብዬ ብልህ ሁን ደግ
ዛሬም ተመልሰህ ጥሬ
እኔስ በቃሃኝ ዛሬ
ላልመልስህ መክሬ
ሊታወረው ልብህ
መሪም አያስፈልግህ
ዓይነ-ስውርን ይመሯል
ልበ-ስውር ግን ያስቸግራል
እንዴት አድግርጎስ ይመራል?
በል አንተም አንቀላፋ
በልብህ የለ ተስፋ
ግና አንድ ልበልህ
የሆነውን ልንገርህ
ደግሞ ካልደነቆርህ
አዝማሪ ሰማሁ ሲዘምር
በትግራይ በጎንደር
“ስልጡን መሪ” ብሎ ሲል
መንበር ከሰሜን ስትወጣ
ሰልጣኔ ይኸው መጣ::
ስማሃኝ ወይ ወንድም
ጥፋተ-ዳግም
ቸር ተመኝ እንጅ ቸሩን
የሚበጀውን
ደጉን እንድታይ እውነቱን
የሀገር አድገቷን
ተወው እባክህን
አውቆ መተኛቱን።

ደሳላኝ በርሄ desberhe@gmail.com